# Ethiopian Meteorology Institute

## Health-Meteorology Bulletin



**The product of Biometeorology and insurance desk**

**Bulletin Type:- Seasonal**

**Issued data**: - 01/06/2025

**Valid until**: - 30/09/2025

**May 2025**

©*Ethiopian Meteorology Institute*

**Tell**: 251(0)11 6615779

**Fax**: 251(0)11 6625292
**P.O.Box** 1090


**Website:**
http://www.ethiomet.gov.et/

**Telegram**:
https://t.me/BiometService


# 1. የበልግ 2025 ወቅት የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ያሳድረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የበልግ 2025 ወቅት በተለይም በማርች ወር ላይ የምዕራብ እና የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ሱማሌ፣ ምስራቃዊ ጋምቤላ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ እና የሲዳማ ክልል በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ለወባ ትንኝ መራባት በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ምቹ የአየር ጠባይ የነበረ ሲሆን በኤፕሪል እና በሜይ ወራቶች ላይ ግን በተለይም በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሲዳማ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና የሱማሌ ክልል አካባቢዎች ላይ ለወባ ትንኝ መፈጠር እና ስርጭት ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ ምቹ የአየር ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 1ሀ)፡፡


በሌላ በኩል ባሳለፈነው የበልግ ወራት የነበረው የሙቀት ተፅዕኖ በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ለሰውም (ካርታ 8) ሆነ ለእንስሳት ተስማሚ እንደነበረ የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ሆኖም ግን በተወሰኑ የጋምቤላ፣ የአፋር፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ እና የሰሜን ሱማሌ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ እና አጎራባች የምዕራብ አማራ ዝቅተኛ በታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ የነበር በመሆኑ በሰዎችም ሆነ በእንስሳት ጤንነት ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 1ለ እና ሐ) ፡፡




ካርታ1፣ ከፌብርዋሪ እስከ ሜይ 2025 ለወባ በሽታ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ የነበሩ አከባቢዎች




ካርታ 1ለ ፣ ከፌበርዋሪ እስከ ሜይ 2025 የነበረው የአየር ጠባይ በሰዉ ልጅ እንቅስቃሴ ያሳደረዉ ተጸዕኖ




ካርታ 1ሐ ፣ ከፌበርዋሪ እስከ ሜይ 2025 የነበረው የአየር ጠባይ በእንስሳት ጤንነት ያሳደረዉ ተጸዕኖ

## 2. በመጪው የክረምት ወቅት የሚኖረው የአየር ጠባይ በጤና ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ክረምት 2025 ወቅት የሚጠበቀው ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በጤና ላይ ሊያሳድር የሚችለውን የተጽዕኖ ትንበያ ስንመለከት፡ ዝቅተኛ እና መካካለኛ መልከዓ ምድራዊ ከፍታ ባላቸው በምዕራብ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ ኦሮሚያ ክልል፣ በድሬዳዋና ሀረር ክልል፣ በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በሲዳማና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በትግራይ ክልል እና በደቡባዊ አፋር ክልል ለወባ ሆነ ሌሎች በትንኝ ለሚተላለፉ በሽታዎች ምቹ የአየር ሁኔታ የሚኖር ቢሆንም ነገር ግን የሚጠበቀው ከፍተኛና ተከታታይነት ያለው ዝናብ በክረምት ወራት ከጥቂት ቆላማ ባህሪ ካላቸው የተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች በስተቀር የወባ ትንኝ የመራባት እደሏ ዝቅተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል። ሆኖም በቀጣይ ክረምት በአብዛኛው የሀገራችን ክፍል ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ስለሚጠበቅ ከጎርፍ ክስተት ጋር ተያይዞ እንደ ለኮሌራ የመሳሰሉ የውኃ ወለድ በሽታዎች መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው ስለሚችል የሚመለከተው አካላትም ሆነ ማህበረሰቡ ተገቢውን የቅድመ ጥንቃቄ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ። በተጨማሪም የመጪው ክረምት ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ አርጥበት የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ በተለይም የወባ በሽታ ስጋት የለባቸው የሰሜንና የምዕራብ አጋማሽ ድንበር ቦታዎች ላይ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች በትኩረት ማከናወነ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ የክረምቱ ተጽዕኖ በቀጣይ በጋ ወቅትም ከፍተኛ የወባ ስጋት የሚፈጥር ስለሆነ ለወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚመለከታቸው አካላትም ሆኑ ህብረተሰቡ ከፍተኛ ዝግጅትና ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

በሌላ በኩል በመጪው ክረምት የሚጠበቀው የከፍተኛ ሙቀትና ወበቃማነት ደረጃ በሰዎችም ሆነ በእሰሳት ጤንነት ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ስንመለከት በተለይም ከጁን እስክ ጁላይ አጋማሽ ድረስ በተወሰኑ በአፋርና በደቡባዊ ሶማሌ ክልል ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ሊኖረው ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላትና ማህበረሰቡ ቅድመ ጥንቃቄ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያስፈልጋለ። ሆኖም በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ግን ከከፍተኛ ሙቀት ጫና አንጻር የከፋ የጤና ችግር የማይኖር ቢሆንም ተጨማሪ የጤና ሚቲዎሮሎጂ ምክረሀሳቦችንም ሆነ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ከኢንስትቲዩቱ ድህረገጽና እንድትከታተሉ እንመራለን።